# አለባብሰው ቢያርሱ . . .

ወርቁ ይሁን 11-28-14

የአንድነት ፓርቲ ጉዳይ አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ ይሉ አይነት እየሆነ ነው፡፡ ዋናዎቹ መሪዎች የነበሩት ኢ/ር ግዛቸውና ኢ/ር ዘለቀ ረዳ ከውጭ ካለው ዲያስፖራ በተደረገብን ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዲሁም በፓርቲው ውስጥ ያሉ የውጭው ዲያስፖራ ወኪሎች ባስነሱት የቡድን መከፋፈልና ተቃውሞ የተነሳ ጫናና ግፊት በስለበረታብን ሀላፊነታችንን ለቀናል እያሉ ነው፡፡ በአዲስ መልክ የራሱን ምርጫ አድርጎ የፓርቲውን አመራር የተቆጣጠረው ወገን ደግሞ ምንም የለም፤ ሰላማዊ ሽግግር ነው የተደረገው ባይ ነው፡፡ ምንም ሆነ ምንም ምርጫ ቦርድ ለአዲሱ አመራር ገና እውቅና አልሰጠም።

አዲሱ አመራር ችግር የለም ሲል የሚገልጸው ብሄራዊ ምርጫው ከፊት ለፊት ስላለ ውስጠ ፓርቲ ችግር እንዳይከሰት፣ አባላቱም ወስጥ መከፋፈል እንዳይነሳ፣ በጥቅል ይዘን እንራመድ የሚል መንፈስ ያዘለ ይመስላል፤ ይሁንና አሁን ጥያቄው ድብብቆሹ እስከ የት ድረስ ያስኬዳል፣ ያራምዳልስ? የሚለው ነው፡፡

ዳግም ምርጫ በአንድነት ፓርቲ ውስጥ ከዓመት በፊት ተካሒዶ ኢ/ር ግዛቸው እና ኢ/ር ዘለቀ ረዲ በከፍተኛ ድምፅ ተመርጠው፣ አመራሩንም አዋቅረው እየሰሩ እያሉ ነው በድንገተኛ ሁኔታ ለፖርቲው ደህንነት ስንል ኃላፊነታችንን ለቀናል ሲሉ ያስታወቁት። ምክንያቱ ደግሞ በውጭ ያለው አክራሪው የዲየስፖራ ተቃዋሚ አባላትና ደጋፊዎች ገንዝብ እያዋጡ ስለሚልኩ ብቻ በሀገር ቤት ያለውን የአንድነት ፖርቲ አመራር (ኢ/ር ግዛቸውን ጨምሮ) እኛ በምንላችሁ ሀሳብና መንገድ ካልሄዳችሁ የምንለውን እርዳታ እናቆማለን ማለታቸው መሆኑ ተገልጷል።

አንድነተ ፖርቲ በሀገሪቱ ሕግ መሰረት ተመዝግቦ የሚሰራ፣ አመራሩና አባላቱም ሀገር ውስጥ የሚገኙ እንደመሆናቸው መጠን በፖርቲው የአመራር/አሰራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ጉዳይም ሆነ መጪውንም ምርጫ በተመለከተ ቁልፍና ወሳኞቹ በሀገር ውስጥ ያሉት ፓርቲዎች ናቸው። በዲያስፖራ የሚገኘው ተቃዋሚ የአንድነትን

ዓላማ በመደገፍም ሆነ በአጋርነት ገንዘብ ሊያወጣ/ሊረዳ ይቻላል፡፡ በየትኛውም መስፈርትና አሰራር ወሳኝና ተፅእኖ አሳዳሪ፣ መሪና አስተዳዳሪ እኔ ያልኩት ካልሆነ . . . ወዘተ የሚል ሊሆን አይችልም፤ አይገባውምም። እኔ የምለው ካልተፈፀመ በእኔ እቅድና ስትራቴጂ ካልተመራችሁ በሚል በአክራሪው ዲያስፖራ የተወጠነው የሴራ ንድፈ ሀሳብ በአመራር ውስጥ መከፋፈል በመፍጠር፣ ተቃውሞ በማስነሳት፣ የስም ማጥፋት ዘመቻ በማካሄድ አመራሩ ላይ ብርቱ ጫና በማሳረፍ የራሱን ወኪሎች ወደ አመራር ማምጣቱ እጅግ አደገኛ አካሄድ ሲሆን የፓርቲውን ህጋዊነትም ጥያቄ ውስጥ እንዲወድቅ አድርጎታል።

ስልጣን መልቀቅ መለመድ ያለበት የዲሞክራሲ ባህል ሲሆን *ውሳኔያቸውን እናከብራለን፤ እናደንቃለን።* በማለት የገለፁት፣ ከአዲሱ የአንድነት ፓርቲ አመራሮች መካከል አቶ አስራት አብረሀም እና ም/ፕሬዚዳንቱ አቶ ግርማ ሰይፉ ሲሆኑ *ለውጥ አስፈላጊ በመሆኑ ጫናና ግፊቱን የፈጠርነውም እኛ ነን* ብለዋል። በስብሰባውም ላይ ይኸን አካሄድ የተቃወሙ ክፍሎች እንደነበሩም አልሸሸጉም። አቶ አስራት ጫና ቢደረግባቸውም መቀጠል ይችሉ ነበርም ማለታቸው በወቅቱተዘግቧል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተደረገው ምርጫና የአመራር ለውጥ ድንገተኛ በመሆኑ የፕሬዚዳንቱን መልቀቅ የተቃወመው ክፍል ሕገ ፓርቲውን ጠቅሶ አቤቱታውን ለምርጫ ቦርድ ያቀረበ ሲሆን ምርጫ ቦርድም ይኸንኑ መነሻ በማድረግ አዲስ ለተመረጠው አመራር ሕጋዊነት አልሰጥም፤ እውቅናም የለውም ሲል አስቷውቋል፡፡

ሕጋዋነት ከተነፈገው አካል እንቅስቃሴ ለማድረግ የማይችል መሆኑ ቢታወቅም አዲሱ አመራር ግን እንቅስቃሴውን ቀጥሎአል። አቶ አስራትም ሆኑ አቶ ግርማ ሰይፉ በዲያስፖራ ያለው ደጋፊና አባል ገንዘቡን እስካዋጣ ድረስ በሀገር ቤት ባለው የፖለቲካው እንቅስቃሴ ላይ ያገባቸዋል ተፅእኖ ማሳደርም ይችላሉ ነው የሚሉት። ዋንኛውና ወሳኙ ሀይል በሀገር ቤት ያለው አባል ሲሆን በምርጫም ሆነ ድምፅ በመስጠት ተሳታፊው እሱው ሁኖ ባለበት ሁኔታ በብዙ ሺህ ኪ.ሜትር ርቀት ላየ የሚገኘው የዲያስፖራ አባልና ደጋፊ ገንዘብ ስለሚያዋጣ ወይንም ስለሚልክ ብቻ *አጀንዳ የሚቀርፅና እኔ ባልኩት መሰረት ብቻ መሄድ አለባችሁ* ብሎ የአመራሩን እጅና ሀሳብ መጠምዘዝ ከቻለ ፓርቲው የሚመራው መሬት ላይ ባለው ተጨባጭ

ሁኔታና በሀሳብ የበላይነት ሳይሆን በጥገኝነትና ከውጭ በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ ነው ማለት ነው፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ፓርቲውና አባላቱ ነጻነት የላቸውም ማለት ነው። ይኸ ማለት፣ በሌላ መልኩ ማንኛውም በብዙ መቶ ሺዎች ገንዝብ ሊያወጣ ወይንም ሊሰጥ የሚችል ኃይል ሁሉ ፓርቲውን በራሱ የሀሳብ ፍሰትና የፖለቲካ ግብ በመናጆነት ሊመራው ይችላል ማለት ነው፡፡ አደጋ ነው አለ ዘሩ ሞላ።

ይህ ጉዳይ ለአገራችን ፖለቲካ አዲስ አይደለም። በኢትዮጵያ ተቀዋሚ ፖለቲካ ፖርቲዎች ዘንደ ስር ሰዶ እስከዛሬ የዘለቀ ዋነኛ (የጋራ) ችግር ሲሆን በውጭ ሀሳብና ገንዘብ መመካት፣ እርዳታን በመተማመን ደረት መንፋት፣ የጥገኝነት መጣባት ክፉ በሽታ እና የመሳሰሉት በየፓርቲዎቻችን ደም ስር ውስጥ ከጶዝ በላይ ተሰራጭተው እንመለከታለን። *ገንዘብ ስለምንሰጣችሁ እኛ ያመንንበትንና መሆን አለበት የምንለውን የፖለቲካ መስመርና የትግል አቅጣጫ ብቻ ነው መከተል ያለባችሁ* በሚል በሀገር ቤት ያለውን በመሳሪያነት ለመጠቀም ነው ፍላጎታቸው - ዲያስፖራዎቻችን። የሀገር ቤቱ ተቃዋሚ ቡድንና አመራር አባላቱም የራሳቸው ነፃነት የሌላቸው፣ በከፋ ተፅእኖ ስር የወደቁ፣ ለውጭ አክራሪ ዲያስፖራ ጥገኞች ያደሩና በባርነት ስር የሚዳክሩ፣ እንኳን ነፃ ሊያወጡ ለራሳቸውም ነፃነት የሚያወጣቸው ክፍል የሚፈልጉ ድኩማን ሆነው ይገኛሉ። የፖለቲካ ተቃዋሚው የትግል አጀንዳ (ድሮም ሆነ ዘንድሮ) የሚቀረጸው፣ ውይይት የሚደረግበትና ተግባራዊ ትሆን ዘንድ የሚተላለፈው በፅንፈኛው ዲያስፖራ ተቃዋሚ ኃይል መሆኑም ከታወቀ ሰነባብቷል።

እዚህ፣ ሀገር ቤት ያለው ተቃዋሚ ራሱን ችሎ ያልቆመ፣ በጥገኛነት በሚያገኘው ገንዘብ (በተለይ ምርጫን ተከትሎ) የሚንቀሳቀስ፣ በምርጫውም ስም የሚመጣው ገንዘብ ተቁዋዳሽና ተቀራማች እንጂ በራሱ በቅቶ ለመንቀሳቀስ የሚችል አይደለም፤ ሆኖም አያውቅም፡፡ ሁሌም ግርግር ለመፍጠር የሚሞክሩት ምርጫ ሲመጣ/ሲቃረብ ብቻ እንጂ ከምርጫ በፊት ባሉት የአዘቦት አመታት የት እንዳሉ እንኳ የማይታወቁ ናቸው፡፡ ይሄም አንዱ አሳፋሪው ገፅታቸውና ድርጊታቸው ነው፡፡ ግልፅና የጠራ ብሄራዊና ሕዝባዊ አጀንዳ የላቸውም፤ የፓርቲና የፖለቲካ ትግል እውቀቱ፣ ልምዱ ብቃትና ችሎታው ጭርሱንም የላቸውም።

በተቃዋሚነት ስም የተመዘገቡ 70 እና 80 ፖርቲዎች ምርጫ በደረሰ ቁጥር አለን ይላሉ። ምርጫ ሲደርስ ድምፃቸው ይሰማል፤ ማናቸውም የት እንደነበሩ፤ ምን ሲያደረጉ እንከረሙ፤ ዓላማቸው፣ ግባቸው፣ ፕሮግራማቸው . . . ምንድነው? አንዱ ፖርቲ ከሌላው በምን ይለያል? ምንም የሚታይም ሆነ የሚታወቅ ነገር የለም። ምርጫ ሲደርስ ብቻ ግዜውን ጠብቀው ገዥውን ፖርቲ የሚተቹ፣ የሚወቅሱ . . . ባጭሩ ምንም አይነት አገርንና ህዝብን ለመምራት የሚያስችል አቅም ሳይኖራቸው በባዶ ሜዳ አካኪ ዘራፍ የሚሉና ምድር የምትጠባቸው ተቃዋሚዎች ሞልተዋል፡፡

የሚወቅሱና የሚተቹትን ነገር ሊተካ የሚችል አማራጭ ፖሊሲ አያቀርቡም፤ ሕዝብ እንዲያየው አያደርጉም፤ ብቻ ምርጫን ተከትለው ረገኸም ምላሶቻቸውን ይወነጭፋሉ፤ *ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው* እንዲሉ ባልሰሩበት፣ ባልደከሙበት አንዲትም የሀሳብና የተግባር አስተዋጽኦ ባላደረጉበት፣ ሌሎች የሰሩትንና የደከሙበትን ልፋትና ትጋት ለማጣጣል ሽሚዛቸውን አጥበውና ተኩሰው ወደ አደባባይ ብቅ ይላሉ፤ አያፍሩም።

እንዲህ ነወይ ለሀገርና ለሕዝብ የሚቆመው፣ የሚሰራውስ? ደግሞስ የፖለቲካ ተፎካካሪ መሆንስ ትርጉሙ የሀገርን ልማትና እድገት መቃወም ነው? እንዴትስ ሊሆን ይችላል? እንዳለ መታደል ሆኖ አጀንዳው ልማት የሆነ አንድም የቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት የለንም። የተሰራውን መልካምና ታላላቅ የሀገር ልማት፣ እድገት፣ ስኬትና ለውጥ ጠብቆ የበለጠ ለማሳደግ የሚሰራ፣ ክፍተት ካለ የሚሞላ፣ ሊያግዝና ሊረዳ የሚችል፣ ልዩነቱን በልዩነት ይዞ ለሀገር በጋራ ለመስራት የተዘጋጀ ተቃዋሚ ኃይል አይደለም ያለን። ያለን ከዚህ በተቃራኒው ተቆም አውዳሚ ወገን ነው፤ አገር ስትለማ ከሚያይ ሞቱን የሚመርጥ ሀይል።

በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭም ያለው ጥገኛ ሀይል በጐጠኝነት፣ በጎሳ ጥላቻ የተመረዘና የተበከለ፣ በቀል የተጠማና በፍጹም አምባገነንት፣ ጀብደኛነትና እብሪት የሚዋኝ ነው። ስለዲሞክራሲና ሰብአዊ መብት የሚያወራ ግን ደግሞ ዲሞክራሲንና ሰብዓዊ መብትን የማያውቅ፣ ልዩነትንና ውበትን የጥንካሬ ምንጭ አድርጐ የማይቀበል፣ *እኔ ብቻ ነኝ ትክክል ሌላው አይመለከተውም፤ አያገባውም፤* የሚል ተቃዋሚ ነው ያለው፡፡

በዚህ መልኩ እንዴትና በምንስ ሁኔታ በጋራ ስለሀገር ማሰብ እንደሚቻልም ያስደምማል። ተቀዋሚው በውድቀት ላይ ውድቀት እየደረበ አንዷትም ለሀገርና ለሕዝብ የሚበጅ ቁም ነገር ሳይሰራ እድሜውን የፈጀው በወሬና በአሉባልታ፣ በመናናቅ፣ በጥላቻ፣ ሌላውን በማንኳሰስ፣ በእኩይና መሰሪ ሴራ ተጠምዶ ነው። ይኸ አካሄድ ሀገርና ትውልድ ገዳይ ከመሆን ያለፈ ለማንም እንደማይበጅ ሲነገራቸው እንኳ ለመስማት የተዘጋጁ አለመሆናቸው ደግሞ የበለጠ ያሳስባል።

አሁን ያለውም፣ ወቅታዊውና አጠቃላይ የተቃዋሚው የፖለቲካ ጐራ ከሀገር ቤት እስከውጭ የተበከለውም በዚህ አደገኛ ሀገር አጥፊ መርዝ ነው። ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የትም ዓለም ላይ ባሉ ሀገራት የተለያዩ ተቃዋሚ ፖርቲዎች አሉ፡፡ የቱንም ያህል በራሳቸው ውስጥና ከገዥው ፖርቲ ጋር  ልዩነት ቢኖራቸውም የሀገራቸውን ብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት፣ ሰላም፣ እድገት ወዘተ በተመለከተ ተቻችለው በጋራ በመቆም ይሰራሉ እንጂ እንደኛዎቹ ነጋ ጠባ ጥፋትና ውድቀትን፣ እርስ በእርስ መባላትን አጀንዳ አድርገው በፍፁም ጥላቻ ተሰንገው አይራመዱም፡፡

ብዙዎቹ ችግሮችን ከነመፍትሄያቸው ያቀርባሉ እንጂ አንድ ሺህ አንድ ችግር በመደርደር፣ በማጥላላት ብቻ ግዜያቸውን አያባክኑም፤ ጥላቻ እያረሱ ጥላቻ አይዘሩም፤ የሀገራቸውንና የሕዝባቸውን ጥቅም ለውጭ ሀይሎች አሳልፈው በመስጠት ከሕዝባቸው ይልቅ በውጪ መንግስታት አያመልኩም፤ አይተማመኑም፤ በአሽከርነትና በተላላኪ ሎሌነት አይሰማሩም፤ የህዝብ ነጻነትን ለግል ጥቅምና ለዘመናዊ ባርነት ሲሉ አሳልፈው አይሸጡም።

እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ጥቂቶች ግን ሁሌም በየሀገሩ ለውጪ ሀይሎች ጥቅም መከበር ሲሉ በቅጥረኛነት ይሰማራሉ፡፡ የህዝብና የሀገር ጥቅምና ክብርን ይሸጣሉ፤ ከሀገራቸው ዜግነት በላይ በውጭ ዜግነታቸው ይኮራሉ፤ ይመጻደቃሉ፤ በውጭ ሀይሎች ተደግፈው ወደ ስልጣን ለመውጣት ይቃትታሉ፤ ያሴራሉ፤ የተሳካላቸው በየሀገሩ የታዩ ቢሆንም አልዘለቁበትም፤ ቆይታቸውም ሆነ እድሜያቸው አጭር ሁኖ ታሪካቸው በውርደት ተደምድሟል።

አንድነት ፖርቲ ውስጥ የተፈጠረው የፖለቲካ ትርምስምስና መመሰቃቀል፣ ግትር የፖለቲካ መስመር፣ እኔ ብቻ  የሚል ትምክህትና የበላይነት ስሜት፣ ሌሎችን

አሳንሶ የማየትና የመገመት የጠባብነት ስሜት፣ በጥገኝነት፣ በውጪ ኃይሎች፣ ፍላጎትና መስመር የመመራት መሰረታዊ ችግሮች ናቸው፡፡

የብሄራዊ ምርጫውን እየተቃረበ መምጣት የተረዳው የውጪው ዲያስፖራ የአመራር ለውጥ መደረግ አለበት ብሎ የወሰነው የራሱን የትግል ስልት ተግባራዊ ለማድረግ የሕዝብ አመፅ ለማጋጋም እንደሆነ ይታወቃል። ይህ አካሄድ ትላንትም ያልበጀ፤ ዛሬም ወደፊትም የማይበጅ፣ ለሀገርም ለሕዝብም የማይጠቅም፣ ኪሳራ እንጂ ትርፍ የሌለው መንገድ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ባጠቃላይ፣ ተቃዋሚው ከጥገኝነት ነፃ መውጣትና ከኪራይ ሰብሳቢነት አባዜው መላቀቅ አለበት፤ ሳይውል ሳያድር አገር መምራት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ጠንቅቆ ሊረዳ ይገባዋል፤ አገር በእልህ፣ በብልጣብልጥነት . . . አይመራምና። አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ እንዲል ስነቃላችን ከወዲሁ መንቃት አለባችሁ ማለት እወዳለሁ።